በቱሪዝም ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት ሪፖርት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ 2015

<u>አዲስ አበባ</u>

ማውጫ

		ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	
1.1.	የጥናቱ ዳራ	
1.2.	የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት	
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	
ክፍል ሁለት	በቱሪዚም ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ	
ክፍል ሶስት	የጥናቱ ስነ-ዘዴ	
3.1.	የጥናቱ ወሰን	
3.2.	የዝግጅት ምዕራፍ	
3.3.	የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች	
3.4.	የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ	
3.5.	የጥናቱ ተግዳሮቶች	
3.6.	የጥናቱ ውስንነቶች	
ክፍል አራት	ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና	
4.1.	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት	
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	
4.5.	የንብረት አስተዳደር	
4.6.	የግዥ አስተዳደር	
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	
4.9.	የፕሮጀክቶች አስተዳደር	
4.10.	ኦዲትና ቁጥጥር	
4.11.	የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና	
ክፍል አምስት	ምክረ-ሀሳቦች	
	ማጣቀሻ ፅሁፎች	

ክፍል አንድ፦ መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ወንጀል ሲሆን፤ በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል ችግር ነው፡፡ ሌላው ሙስና በአደራ የተሠጠን ኃላፊነት ለግል ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ማስገኛ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ነው፡፡ የሙስና መንሠራፋት የህግ የበላይነትን ያጣምማል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያቀጭጫል፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያዳክማል፣ የኢንቨስትመንት ፍሰት ይገታል እንዲሁም ሥርዓት አልበኝነት እንዲንሰራፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች ፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት አስፈላጊ ህጎች እንዲወጡ በማድረግ እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጅቶችና አሰራሮች በዘርፍ ደረጃ ሲተገበሩ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነታቸውን በየወቅቱ በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁ በማድረግ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በዘርፍ ስር ሊከሰቱ የሚችሉ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፤ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር እና የመረጃ አያያዝ ጥራት ችግር ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሠራሮች እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በቱሪዚም ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1.2. የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 24 መሰረት ለቱሪዝም ዘርፍ (ለቱሪዝም ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

የቱሪዝም መስህቦችን ከማልማት እና መሰረተ ልማቶችን ከመገንባት አንጻር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለቱሪዝም ጉብኝት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ይዘረጋል፡፡ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲሁም በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙ የማደረግ ሥራን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ እንዲሁም ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የሀገሪቱን የቱሪዝም እና የኢኮ-ቱሪዝም አለኝታዎችና መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ እንዲሁም ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፡፡

ደረጃ እና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፡፡ በተጨማሪም ሥልጣኑ በግልጽ በሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር ከመፍጠር እንዲሁም የዘርፉን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዎ ከማጎልበት አንጻር የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት የሀገሪቱን የቱሪዝም ሀብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፣ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን በመፍጠር የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲያድግ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም የቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፡-

የቱሪዝም ዘርፍ ተቋማትን የአሰራር ስርዓት ከሙስና ስጋት አንፃር በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ትንተና ማካሄድ ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡-

የቱሪዝም ዘርፍ ተቋማትን፥

- የአሠራር ስርዓቶች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

ክፍል ሁለት፥- በቱሪዚም ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ

የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ የዓለም ኢኮኖሚ አካል ሆኗል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ እንደሚያመለክተው በ2022 ከ900 ሚሊዮን በላይ ቱሪስቶች በአለም አቀፍ ደረጃ ተጉዘዋል፡፡ በ2021 ዓም በአለም አቀፍ ደረጃ ጉዞ እና ቱሪዝም ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) የነበራቸው ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ወደ 5.8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገደማ ነበር፡፡ ይህ ዘርፍ በ2020 መጀመሪያ ላይ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ ክፉኛ ተጎድቷል፡፡ በ2020 ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ ወደ 2.28 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ አግኝታለች፡፡ በወቅቱ ይህ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 2.1 በመቶ ድርሻ ነበረው (UNWTO, 2022)፡፡

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ውስጥ ማጭበርበር እና ሙስና በሰፊው የተንሰራፋ ሲሆን፣ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ዋነኛ ተጠቂ ናቸው፡፡ ሙስና የታክስ ገቢ መጭበርበርን/ማጣትን፣ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ስም/ዝና መጥፋትን፣ የእንግዳ እርካታ ማጣትን እና ሌሎችንም ስለሚያመለክት የኢኮኖሚ እድገታቸውን በቱሪዝም ልማት ላይ ለመሰረቱ ሀገራት ትልቅ የጭንቀት ምንጭ ነው (Harris, 2012)፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ ከሚታዩ የሙስና ክስተት አመላካቾች መካከል፥- ከመጠን በላይ ክፍያ/ጉቦ በመጠየቅ በቱሪስቶች ላይ ያነጣጠረ የገንዘብ ማጭበርበር፣ ከአገልግሎት ደረጃ እና ከዋጋ አንፃር በቱሪስቶች ላይ የሚደርስ መድልዎ/በደል፣ በተሳሳተ ወይም ግልጽነት በሌለው መረጃ ቱሪስቶችን ላልተጠበቁ ወጪዎች (hidden costs) መዳረግ፣ አጠራጣሪ የግብይት ዘዴዎችን (suspicious transaction practices) በመጠቀም የታክስ ማጭበርበር/ገንዘብን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን የሚያግዙ ደንቦችን ተግባራዊ ካለማድረግ የሚመነጩ የዘላቂነት (sustainability) እና የማህበራዊ ኃላፊነት ውድቀቶች፣ ከባለስልጣናት ብልሹ አሰራር የሚመነጩ ቱሪስቶችን የማይመጥኑ

ዝቅተኛ የጤና እና የደህንነት ደረጃዎች እንዲሁም ቱሪስቶች የወንጀል ሰለባ የሚሆኑበት እና ከባለሥልጣናት ድጋፍ የሚሹበት አጋጣሚዎች ይጠቀሳሉ (Papathanassis, 2016)።

በሙስና እና በቱሪዝም መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ እርስ በርስ የሚጋጩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል። እንደ Méon and Sekkat (2005) ጥናት መሰረት ሙስና በቱሪዝም ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። አጥኚዎቹ ሙስና "የአስተዳደር ገጽታዎች ውጤታማ ባልሆኑባቸው" አገሮች ቅልጥፍናን ለመጨመር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለው ተከራክረዋል። የዚህ ፅንሰ-ሀሳብ ደጋፊዎች ዝቅተኛ የመንግስት ጥራት (low quality of government) ባለበት ሁኔታ በአላስፈላጊ ቢሮክራሲዎች ምክንያት የሚፈጠረውን እንግልት ለመቀነስ ሙስና አስፈላጊ ነው ያምናሉ። ነገር ግን ከዚህ አንፃር መታወቅ ያለበት የሙስና/የጉቦ ክፍያ ተጨማሪ ወጪ በተጠቃሚው ስለሚሸፈን የተፈለገውን አገልግሎት ዋጋ በማናር ተጠቃሚው ላይ አላስፈላጊ ጫና ማሳደሩ ነው።

በአንፃሩ፣ በርካታ ጥናቶች ደካማ የህግ አስከባሪ አካላት፣ ፍሬያማ ያልሆነ መንግስት እና የፖለቲካ ብጥብጥ በቱሪዝም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ደርሰውበታል። ለአብነት ያህል Assaf and Josieassen (2012) እና Yap and Saha (2013) ሙስና ባለበት ሁኔታ አገሮች ባህላዊና አካባቢያዊ ቅርሶች ቢኖሯቸውም የቱሪዝም ኢንዱስትሪያቸውን ማጎልበት አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል። Poprawe (2015) በ100 ሀገራት ላይ ባደረገው ጥናት ሙስና መጨመር በቱሪዝም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳለው አረጋግጧል። ይህ ጥናት እንደሚያሳየው የሙስና በአንድ ነጥብ መቀነስ ከ6-7% ከፍ ያለ የቱሪስት ፍሰት እንዲኖር አድርጓል። በተመሳሳይ Das and Dirienzo (2010) የሙስና መቀነስ በ119 አገሮች የቱሪዝም ተወዳዳሪነት ላይ በጎ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ዘግበዋል።

አንድ አገር ውስጥ ጉቦና ማጭበርበር የተለመደ ከሆነ ማኅበራዊና ባህላዊ ገጽታዋን ሊጎዳ እና የቱሪዝም ተወዳዳሪነቷን ሊያደናቅፍ ይችላል (Das & Dirienzo, 2010)። ይህም አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚያሳድር ጎብኚዎች አማራጭ መዳረሻ እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል። ሙስና የንግድ ሥራ ወጪን (cost of doing business) ከፍ በማድረግ በቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ እንቅፋት ይፈጥራል (Tonsun & Timothy, 2001)። ሙስና ሰዎች ስለሚጎበኟቸው ሀገራት ያላቸውን ምስል (image) ይሸረሽራል፣ በደህንነታቸው እና በጉዞ ወጪያቸው ላይም ጥርጣሬን ይፈጥራል። በአጠቃላይ Poprawe (2015) እንደሚለው፣ ሰዎች አነስተኛ ሙስና ወዳለባቸው አገሮች መሄድን ይመርጣሉ - በተለይም ሙስና ካልተለመደባቸው አገሮች የመጡ ከሆነ። እንደ ጉቦ ያሉ የሙስና ዓይነቶች ከታክስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ተጨማሪ ወጪዎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ። እንደ Lv and Xu (2017) ገለፃ ቱሪስቶች ሙስና የሚያመጣውን ተጨማሪ ወጪ (ይህን 'ግብር') ለመክፈል አይፈልጉም።

በመንግስት ደረጃ ሙስና በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ሙስና ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑትን የንግድ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ይበጥሳል። በሙስና የተዘፈቁ የመንግስት ኃላፊዎች ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የተመደቡ ሀብቶችን ለግል ጥቅማቸው ሊያውሉ ይችላሉ። በሙስና የተዘፈቀ መንግሥት በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን አስፈላጊ ጉዳዮች ለመፍታት ተነሳሽነት ላይኖረው ይችላል። በተጨማሪም ሙሰኛ መንግስታት የቱሪዝም ኢንደስትሪውን የሚያግዙ ደንቦችን ተግባራዊ ላያደርጉ ይችላሉ (Ekine, 2018)።

ስለሆነም ሕግ አውጪዎች እና እንደ ንግድ ምክር ቤቶች፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተቆጣጣሪዎች ወይም አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂዎችን የመንደፍ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት የቱሪዝም ገቢዎችን ለመጨመር ከፈለጉ በመጀመሪያ ሙስናን መዋጋት አለባቸው:: ሙስናን በብቃት መፍታት ማለት ሁሉን አቀፍ እና ትርጉም ባለው መልኩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የሥነ ምግባር ደንብና ፖሊሲዎችን ማክበር፣ የማህበራዊ ኃላፊነት ፖሊሲዎችን እንዲሁም የጥቆማ/መረጃ አመንጪ (whistle-blowing) ስርአቶችን መተግበር ማለት ነው (Maria et al., 2022):: በPapatanassis (2016) ጥናት መሰረት ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውን በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ለመሠረቱ አገሮች ዘርፈ-ብዙ ወይም በአገር-አቀፍ ደረጃ ሙስናን ለመዋጋት/ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ ዘርፍ-ተኮር የፀረ-ሙስና ድጋፍ ሰጪ መዋቅሮችን መዘርጋት የበለጠ ውጤታማ (እና ተጨባጭ) ሊሆን ይችላል::

ክፍል ሶስት፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ

3.1. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል የቱሪዝም ሚኒስቴር እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑ ሁለት ተቋማት (የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣንና የኢትዮጵያ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን) ላይ ነው::

3.2. የዝግጅት ምዕራፍ

በመጀመሪያ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 10 የትኩረት ርእሰ-ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ መሰብሰቢያ ቼክ-ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ 10 ርእሰ-ጉዳዮች ማንኛውም የመንግስት ተቋም ሊተገብራቸው የሚገቡና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አሰራሮች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው:: እንደሚታወቀው ተቋማት ከተቋቋሙበት ዐላማ አንፃር የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕሪ አላቸው:: ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተቋማቱ ልዩ ባሕሪ ሊመነጩ የሚችሉና የመለያየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸውን የሙስና ስጋቶች ለመለየት አንድ ተጨማሪ ርእሰ-ጉዳይ ተካቷል::

በመቀጠልም በተዘጋጀው ቼክ-ሊስት ዙርያ ለጥናት ቡድን አባላት (መረጃ ሰብሳቢዎች) ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎች ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ ፈጥረዋል::

3.3. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው:: ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ቼክ-ሊስት፡- የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ

የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ የተቋማት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የተሞረኮዘ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

ሰነዶች፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡፡

የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡- ከ10ሩ ርዕሰ-ጉዳዮች ጋር ታያያዥነት ያላቸውን ወይም በቀጥታ በቼክ-ሊስት ውስጥ ያላተካተቱትን የሙስና ስጋቶች በጥቂቱ ለመዳሰስ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

3.4. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ቡድን መሪዎች አስተባባሪነት የጥናት ቡድን አባላት ከየተቋማቱ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በዘርፍ ደረጃ በማጠቃለል ትንተና አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ አማካሪዎች በበኩላቸው የሙስና ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡

3.5. የጥናቱ ተግዳሮቶች (Challenges of the study)

ጥናቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የተወሰኑ የተቋማት ኃላፊዎች/ባለሙያች ቀጠሮ አለማክበር እና የጥናት ቡድን አባላትን ማመላለስ፤
- በአንዳንድ ተቋማት የዲኤዲ ምደባ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ የተሟላ መረጃ ለማግኘት አለመቻል፤
- የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

3.6. የጥናቱ ውስንነቶች (Limitations of the study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት ቀድሞ በተመረጡና ለሁሉም ተቋማት ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰራ ከመሆኑ አንፃር የዘርፉን የሙስና ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡

በሌላ አገላለፅ በዚህ ጥናት ያልተለዩ ሌሎች የሙስና ስጋቶች በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን በቀጣይ ለሚሰሩ ጥልቅ ጥናቶች እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መናገር ይቻላል፡፡

ክፍል አራት፦ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የቱሪዝም ዘርፍ የስራ አፈጻጸም እና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ክፍሎቹ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል፣ የክልል እና የፌደራል ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የሥነምግባር ፖሊሲዎች መገምገም እና ማዘመን፣ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የስነምግባር ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የህግ መስፈርቶች ላይ ከፍተኛ አመራሮችን ማማከር፣ ለአመራር እና ሰራተኞች በሥነምግባር ደረጃዎች (ethical standards) ላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለትን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መምከር ይገኙበታል፡፡ የሥነምግባር ክፍሎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

የቱሪዝም ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት ሁለቱም ተቋማት ሙሉ ለሙሉ በተፈቀደው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደብ የሰው ኃይል ያሟሉ ሲሆን፤ በቱሪዝም ሚ/ር ግን ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ አንድ ዳይሬክተር ብቻ እንደተመደበ ከቅጥር ደብዳቤዎች እና ከተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም የሁለቱ ተጠሪ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የራሳቸው በጀት የተመደበላቸው ሲሆን፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን የበጀት ምደባን በሚመለከት መረጃ አልቀረበም፡፡ የሶስቱም የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ እንዳላቸው ከቀረቡ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር፣ በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙት ሶስት ተቋማት ውስጥ ሁለቱ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሚሟላታቸው በበጎ ጎን የሚታይ ሲሆን ቀሪው አንድ ተቋም ግን ይህን አለሟሟላቱ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም ከአንዱ ተቋም በስተቀር በሌሎቹ ሁለት ተቋማት ውስጥ የህግ ክፍል ራሱን ችሎ

ተደራጅቶ ይገኛል፡፡ የዘርፉ ተጠሪ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ጥቆማ የሚሰጥበት፣ የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተገበሩ ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን የጥቆማ መቀበያ ስርዓት አለመዘርጋቱ በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ ከተቋቋመባቸው ሁለት ተቋማት ውስጥ በአንዱ ብቻ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት ያለ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ግን ይህ አሰራር ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የሚ/ር መስሪያ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአንድ ዳይሬክተር ብቻ እንደሚንቀሳቀስ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ተገቢውን የሙስና ስጋት ግምገማ በማካሄድ አደጋን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከል ስልት ለመንደፍና የቁጥጥር ስርአትን ለማዳበር የሚያስችል አደረጃጀት እንደሌለው ጠቋሚ ነው፡፡ ለክፍሉ የተመደበ በጀት መኖሩን የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩም ለስራ የሚያስፈልገውን በጀት ምናልባት በአመራሩ መልካም ፈቃድ ብቻ የሚያገኝበትን አጋጣሚ ስለሚፈጥር ክፍሉን ለአላስፈላጊ የአመራር ጣልቃ-ገብነት ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡
- እንደሚታወቀው የጥቆማ ስርአት የተከሰቱ የሙስና ድርጊቶች እና ብልሹ ተግባራትን ለመለየት፣ ለማጣራት እና ተገቢውን የህግና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ አይነተኛ የትግል መሳሪያ ነው፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ ይህ ስርዓት አለመዘርጋቱ በስውር የሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮች እና የሙስና ድርጊቶች ወደ ወንጀል አድገው ጉዳት ሳያደርሱ አስቸኳይ የማጣራት ሥራ በማከናወን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ፣ የጋራ ትንተና ለማካሄድ እንዲሁም የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ለመንደፍ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ የመንግስትን ጥቅም ሊጎዱ የሚችሉ ውሎች በሙስና ድርድር/ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ አንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ሁለቱ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራርን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ስለማካሄዳቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ ቀሪው አንድ ተቋም በሰው ሃብት ልማት የስራ ክፍል ላይ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄደ ቢሆንም በጥናቱ መሰረት ማሻሻያዎችን ስለማድረጉ ግን መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል የሚጠና ስለመሆኑ እንዲሁም የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ስለማዘጋጀታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በሁለት የዘርፉ ተቋማት ውስጥ የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች እንደሌሉ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአንዱ ተቋም ግን በአበል አከፋፈል ላይ የተሳሳተ ድርጊት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ደርሶ ቀድሞ የመከላከል ስራ እንደተሰራ በውይይት ወቅት የተገለፀ ቢሆንም ይህን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሥነምግባር ጉድለት ምክንያት በአመራሩም ሆነ በፈጻሚ አካላት ላይ ምንም ዓይነት የቀረቡ ክሶች እንደሌሉ ለመገንዘብ ሲቻል፣ የተቋማቱ የህግ ክፍል በፍትሀብሔር እና በወንጀል ጉዳዮች ባለፉት ሁለት ዓመታት ክሶች ስለመመስረቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ቅሬታን በተመለከተም በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት መካከል አንዱ ላይ ብቻ ሁለት ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን ሙሉ በሙሉ (100%) እንደተፈቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በቱሪዝም ዘርፍ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በተቋማቱ የበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማካሄዳቸው፣ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እነኚህ ተግባራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ቅድመ-መከላከል ስትራተጂዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ካላቸው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን ያሳያል፡፡

- በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነምግባር ደንብ ስለማዘጋጀታቸው የሚያመላክት መረጃ አልተገኘም። የሥነምግባር ደንብ አለመኖር የተቋማቱን እሴቶች፣ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና መርሆዎች በተመለከተ አመራርና ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን መሰረት አድርጎ ሥራን ከመስራት አኳያ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡ ፡
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች እንደተሰሩ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። የሙስና ወንጀሎች ከመፈፀማቸው በፊት በመረጃዎች ላይ በመመስረት የሚወሰድ የማስተካከያ/የመከላከል እርምጃ አለመኖር ለሃብት ብክነትና ለደንበኞች እንግልት ሊዳርግ የሚችል የሙስና ስጋት ነው።
- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። ይህም የተቋማት አመራሮች በተቋማቸው ለሚካሄድ የፀረ-ሙስና ትግል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር በቂ ትኩርት አለመስጠታቸውን የሚያሳይ ክፍተት ነው።

4.3. የተቋማት ግልፅነት

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው። የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢመዘገብም የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም። ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እየተገባ መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ መረዳት ይቻላል። ይህም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ይጫወታል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም ግን በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የዕቅድ ግምገማ የሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመለየት በሚያስችል መልኩ ስለመከናወኑ መረጃ አልቀረበም።

በዘርፉ የሚገኙ አብዛኞቹ ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በብሮሸር እና በማስታወቂያ ሰሌዳ ተደራሽ እንደሚያደርጉ በውይይት ወቅት ተገልጿል። በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ተቋም በስተቀር ቀሪዎቹ ሁለቱ በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ በጥናቱ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል። ሆኖም ግን የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ስለመደረጋቸው ከአንዱም ተቋም መረጃ አልቀረበም።

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያሰራጩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ተቋማቱ ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው ግን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ ብቻ መረጃ የሚያሰራጭበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድህረገጽ እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ ሁለቱ ግን መረጃ የሚሰራጭበት ማህበራዊ ሚዲያ ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ ስር በሚገኝ አንድ ተቋም በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ መረጃ አልቀረበም:: እንዲሁም የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም:: ይህም ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል::
- በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት አብዛኛዎቹ መረጃ የሚያሰራጩበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድህረገጽ ለመኖሩ ምንም መረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ከመረጃ ስርጭት አንፃር ለዜጎች በሰፊው ተደራሽ የሆነ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በዘርፉ ውስጥ እጅግ ኋላ ቀር ደረጃ ላይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::
- የዘርፉ ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ሚዲያ (በተለይም የምርመራ ጋዜጠኝነት) ሙስናን ለህዝብ እይታ በማጋለጥ እንዲሁም ያለምንም ተጠያቂነት (with impunity) የሚፈፀሙ ጎጂ ስራዎችን በመዋጋት ረገድ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና አንፃር የመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ አለመሆን የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል::

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግን በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡ ፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ሙዚየም ለማቋቋም ለሚጠይቁ አካላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አለመስጠቱ በ2014 በጀት ዓመት በውጭ ኦዲተሮች በተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ እንደግኝት መገለጹን ተከትሎ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ የነበረን መመሪያ ባሁኑ ወቅት ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማሻሻል እንቅስቃሴ እያደረገ ስለመሆኑ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ግን በጥናቶች እና በዕለት-ተለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች

በመንተራስ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም።

በዘርፉ ስር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ እንዲሁም ፀድቀው የሚወጡ ህጎች እና መመሪያዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ አንድ ተቋም እንዳዘጋጀ በምልከታ የታየ ሲሆን፣ የተዘጋጀው ቻርተር ለተገልጋይ ተደራሽ ስለመደረጉ ግን መረጃ አልቀረበም፡ ፡ በቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ግን የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም።

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ጥናቶችን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ስለማከናወናቸው መረጃ አልቀረበም። በየጊዜው እየተራቀቁ የመጡት የሙስና ስልቶች ነባር ህጎች ያለባቸውን ክፍተት በመጠቀም የሚሰሩ ከመሆናቸው አንፃር ህጎቹን የመፈተሽና የማሻሻል ተግባር እንደመደበኛ የተቋማት የስራ አካል ተወስዶ አለመሰራቱ ለሙስና መከላከል ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጠ አመላካች ነው።
- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አልቀረበም። ይህ አለመከናወኑ በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ በር የሚከፍት ክፍተት ነው።
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር አለመዘጋጀቱ እና የተዘጋጀውም ቢሆን በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አለመደረጉ የተቋማቱ አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።
- በዘርፉ ስር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ውስጥ ፀድቀው የሚወጡ ህጎች እና መመሪያዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። ተደራሽነት ህጎች እና መመሪያዎች ሰራተኞችም ሆነ ተገልጋዮች እንዲመሩባቸው እንዲሁም ድርጊታቸው የሚያስከትለውን ውጤት በግልፅ እንዲያውቁ ካለው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን አለማከናወናቸውን አመላካች ነው።

4.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ከንብረት ርክክብ እስከ ማስወገድ ድረስ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው። ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ

ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል።

በሁሉም ተቋማት እየተተገበረ የሚገኝን የቢን ካርድ እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ አጠቃቀም ስርዓትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ወደተሟላ የአውቶሜሽን ስራ IFMIS ለማስገባት ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ መደረጉም ተረጋግጧል። ከንብረት ቆጠራ ጋር በተያያዘ ሁለት ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እንዳደረጉ በሰነድ ሲረጋገጥ በቀሪው አንድ ተቋም ግን ይህ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በ2014 በጀት ዓመት በሶስቱም ተቋማት ንብረቶች በስጦታ እና በሽያጭ መልክ እንደተወገዱ በሰነድ ተረጋግጧል። ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ ህትመቶችን በአሁኑ ሰዓት ለማንኛውም አገልግሎት እንደማይሰጡ በኮሚቴ በማረጋገጥ አስወጋጅ ኮሚቴ በተገኘበት በማቃጠል እንዲወገዱ አድርጓል። የኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን በበኩሉ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች ግምታቸው ከ426 ሺህ ብር በላይ የሆኑ ላፕቶፖች፣ ዴስክ ቶፖ ኮምፒዉተሮች እንዲሁም ሌሎች የቢሮ ቁሳቁሶችን በእርዳታ/በስጦታ መልክ ሰጥቷል። የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ደግሞ ግምታቸው ከ71 ሺህ ብር በላይ የሆነ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ እንዲሁም ሌሎች የገንዘብ መጠናቸው ያልታወቀ ንብረቶችን በእርዳታ/ስጦታ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡

በአንድ ተቋም ውስጥ የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን መረጃዎች ሲያሳዩ በሌላው ተቋም ግን ይህ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በሁሉም የሚወገድ ንብረቶች ባላቸው ተቋማት ንብረቶቹ ተገቢው ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገላቸው መሆኑን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ ያልተገኘላቸው የዘርፉ ተቋማት አሉ፡፡ የግምገማ አለመኖር ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶች በሙስና ድርድር እንደአላስፈላጊ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ተፈርጀው ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በአንድ የዘርፉ ተቋም ውስጥ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ የንብረት ቆጠራ አለማድረግ በንብረቶች ላይ የሚደረግ የቁጥጥር ስርዓትን በማላላት የመንግስት ንብረት አላግባብ እንዲባክን የሚችልበት ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኗል፡፡

በዘርፉ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ክፍሎች በሚሰበሰብ የግዥ ፍላጎት መሰረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ እንደሚያዘጋጁ፣ በመቀጠልም በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተገምግሞ እና ፀድቆ ወደ ግዥ ኤጀንሲ እንደሚላክ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግዥ አፈፃፀም ላይ ግምገማ ያከናውናሉ፡፡ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የገንዘብ መጠናቸው ከ584 ሺህ ብር በላይ የሆኑ ንብረቶች ግዢ ከዕቅድ ውጭ የፐሮፎርማ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ተከናውኗል፡፡

በሁሉም ተቋማት ከየክፍሎች የሚቀርብ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ ግዥዎች የሚከናወኑ ስለመሆኑ በተደረገ ውይይት ግንዛቤ መወሰዱ ቢገለፅም ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ ግን አልተገኘም፡፡ በሁለት ተቋማት ውስጥ ከግዥ በፊት የገበያ ጥናት አድራጊ ኮሚቴ በማዋቀር ጥናት እንደሚከናወን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በቀሪው አንድ ተቋም ግን ይህ ስለመከናወኑ የሚያመላክት ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ተቋማት የEGP ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ የግዢ ስርአት ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዥ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከ2014 የበጀት ዓመት ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አልነበሩም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ያለዕቅድ የሚፈፀም የፐሮፎርማ ግዥ መኖር የግዥ ዕቅዶች ክፍተት እንዳለባቸው አመላካች ከመሆኑ ባሻገር የውስጥ ቁጥጥርን በማላላት የግዥ ስርዓቱን ለብልሹ አሰራር ሊያጋልጠው ይችላል፡፡
- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ግዥ የሚከናወነው ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ክፍተት በቂ ስቶክ ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በአንዱ የዘርፉ ተቋም ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው፡፡

4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን ፣ ወዘተ ኮሚቴዎች በማቋቋም ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በጂኤጂ ምደባ ላይ 126 ቅሬታዎች ቀርበው ሙሉ በሙሉ ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት በተቋሙ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት በኩል ውጤታማ ስራ መሰራቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተሰበሰቡ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆንም ለማድረግ የሚያስችል ስርአት የተዘረጋ መሆኑና ሕጉን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የስራ ኃላፊዎች ምደባ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሃሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ ማጣራትን በተመለከተ አንዳቸውም የዘርፉ ተቋማት ወደ ስራ እንዳልገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተቋማቱ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ጅምር ስራዎች እንዳሉ ቢገለፅም መረጃውን ማግኘት አልተቻለም፡፡

ስልጠናን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን በርካታ የሥነምግባርና የሙያ ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይም በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የአጭርና ረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ስለመሰጠታቸው በተቋሙ የ2015 ዓ.ም የስድስት ወር ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ውስጥ ተገልጿል፡፡ በቀሪው አንድ ተቋም ግን ስልጠናዎች መሰጠታቸውን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በዘርፉ ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ያለበቂ ችሎታ እና የስራ ልምድ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ሊኖሩ የሚችሉበትን ክፍተት በመፍጠር የመንግስት ሃብት ያላግባብ ጉዳት እንዲደርስበት እንዲሁም ጥራት ለጎደለው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት አለመገንባቱ የቅጥር፣ ዝውውር፣ ምደባ፣ ወዘተ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

- ሙስናን ከውስጥ መከላከል የሚቻለው አመራርና ሰራተኞች የታማኝነት፣ የተጠያቂነት፣ የፍትሃዊነት እና የመተማመን ጠንካራ የሞራል እሴቶችን ካዳበሩ ነው፡፡ የሥነምግባር ስልጠናዎች በዚህ ረገድ ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በዘርፉ አብዛኛው ተቋማት በሥነምግባር ዙሪያ የስልጠናዎች አለመኖር አመራርና ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፉና እንዲታገሉ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው ልክ ከግብ እንዳይደርስ ሊያደርግ የሚችል ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጥልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት፣ በአፍሪካ ህብረት የሙስና መዋጊያ እና መከላከያ ስምምንት እንዲሁም የዓለም አቀፍና የአህጉር አቀፍ የፀረሙስና ስምምነቶችን ተቀብለው በሚፈፅሙ ሀገራት እየተተገበረ ይገኛል፡ ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ሥርዓቱን ባለፉት አሥር ዓመታት ስትተገብር ቆይታለች፡፡ ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን ማስመዝገብ ካለባቸው አካላት መካከል የፌደራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት የሃብት ምዝገባ ማድረግ ከሚገባቸው አመራሮችና ሰራተኞች መካከል በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን 32 በመቶ እንዲሁም በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን 15 በመቶ ሀብታቸውን አስመዝገበዋል፡፡ የቱሪዝም ሚ/ር አመራሮችና ሰራተኞች ሃብታቸውን ስለማስመዝገባቸው ግን መረጃ አልቀረበም፡፡ የሃብት ምዝገባ ስራ በዘርፉ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ አለመደረጉ የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ ሀብቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር እንደ ሙስና ስጋት ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፣ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያፈልጋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት ከሚያካሂዷቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ፣ ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው እንዲሁም ውላቸው ተቋርጦ በክስ ሂደት ላይ የሚገኙ እንዳሉ በሰነድ ተረጋግጧል።

- በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ (የቱሪዝም ሚ/ር በተለያዩ የቱሪዝም መዳረሻዎች እያስገነባቸው ከሚገኙ የልማት ሥራዎች መካከል ግምታቸው አስራ ስምንት ሚሊዮን ብር የሚሆኑ አምስት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቃቸው፣ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ሁለት የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ተቋሙን ወደ 3.4 ሚሊዮን ብር ለሚጠጋ ተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ ያደረጉ መሆኑ፣ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የታሪካዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ፕሮጀክት እና የብሔራዊ ሙዚየም ህንፃዎች ዕድሳትና ምድረ ግቢ ማስዋብ ፕሮጀክቶች የወጪ አፈፃፀም 24 በመቶ ብቻ መሆኑና በቀጣይ ቀሪ ጊዜያት ተጨማሪ ጥረት ካልተደረገ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ላይጠናቀቁ የሚችሉበት የአሠራር ክፍተት ሊያጋጥም የሚችል መሆኑ)፣
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው (የሃላይዲጌ አሰቦት እና ነጭ ሳር ብ/ፓርክ ጽ/ቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች እንደቅደም ተከተላቸው የብር 147,691.73 እና 261,416.03 ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው፣ ከዲዛይን ለውጥ ጋር ተያይዞ በድሬደዋ ከተማ ለሚገነባ የላንድ ማርክ ግንባታ፣ በሰንቀሌ የቆርኪዎች መጠለያ እየተገነቡ የሚገኙ የእደጥበብ ማዕከል እና የመፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ በላሊበላ ለሚገነባ የመጸዳጃ ቤት እድሳት በድምሩ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ በተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ ለኮንትራክተሮች የተከፈለበት)፣
- ውላቸው ተቋርጦ በክስ ሂደት ላይ የሚገኙ (በሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ የካምፒንግ አገልግሎት፣ በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የጎብኚዎች ማዕከል፣ በጨበራ - ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ የጎብኝዎች ማዕከል ቀደም ሲል የተጀመሩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ውላቸው የተቋረጠና በክስ ሂደት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ)፣

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የግንባታ ዲዛይን ዝግጅት ላይ ከሚከሰቱ ክፍተቶች እንዲሁም ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው።
- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ምናልባት ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚ ነው።
- የበርካታ ውሎች መቋረጥ በጨረታዎች ሂደት ላይ ጥርጣሬን ይፈጥራል። ድምዳሜ ላይ መድረስ ባይቻልም የውሎች መቋረጥ መፅደቅ የማይገባቸው ጨረታዎችን ከማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይገባቸው ተጫራቾች እንዲያሸንፉ ከማደረግ ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በዘረጉ ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስና በእጅጉ እንደሚቀንስ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተቋማት ህጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ በየጊዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ኦዲተር የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሠራራቸውን የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በቱሪዝም ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በዘርፉ ያሉ ተቋማት በየዓመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን ከሪፖርቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ አብዛኞቹ የተቋማት አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የማካሄድ ልምድ ያላቸው ለመሆኑም ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ የውጭ ኦዲት ሪፖርትና የተደረጉ ማሻሻዎችን በተመለከተ ግን አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት መሻሻል እንዳለ በቃል ከመግለጽ ዉጪ ለዋና ኦዲተር የተላከውን ሪፖርትና የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎችን የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ዉስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ተቋማት ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን፣ በዘርፉ ስር ያለ አንድ ተቋም ግን ከሥነምግባር ክፍል በተጨማሪ ለህግ አገልግሎት ተደራሽ ማድረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለሌሎች የስራ ክፍሎች ግን የኦዲት ሪፖርት ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ወይም ልምድ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ከተካሄዱ የውጭና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በግኝት የተለዩ የአሠራር ክፍተቶች እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡-

- በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ሥር በሚገኘው የተንቀሳቃሽ ቅርስ ልማት አግዚብሽን ዳይሬክቶሬት ላይ በ2014 በጀት ዓመት በውጭ ኦዲተሮች የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ለሰው ዘር ምንጭ ሙዚየም ግንባታ ለማካሄድ በታቀደበት አራዳ ክ/ከተማ ከሚገኝ ቦታ ለሚነሱ ተነሽዎች ተቋሙ ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ ቢከፍልም ነዋሪዎች እስካሁን ከግንባታው ቦታ ባለመነሳታቸው ግንባታው ስኬታማ አለመሆኑን ገልጿል፣
- በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ላይ በ2014 በጀት ዓመት የተከናወነ የውስጥ ኦዲት ከአስራ ሁለት ሚሊዮን ብር በላይ በወቅቱ እንዳልተወራረደ ገልጿል፣

በአብዛኞቹ ተቋማት የሒሳብ አያያዝ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS - Integrated Financial Management Information System) ለማስገባት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ በውይይት ወቅት ቢገለፅም፣ ይህ አዲስ አሰራር በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የኦዲት ግኝቶች ላይ በመመስረት የተወሰዱ ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ ከሁሉም የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም፡፡ የማሻሻያ እርምጃዎች አለመኖር የተከሰቱ ብልሹ

አሰራሮች እንደገና ለተቋሙ ስጋት የመሆናቸውን አጋጣሚ ስለሚያሰፋ እንደ ትልቅ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል፡፡

- በዘርፉ ተቋማት ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ የፋይናንስ መመሪያ ጥሰትን እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን አመላካች ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡
- በዘርፉ ተቋማት የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህ ሥርዓት የሒሳብ አያያዝ እና ምዝገባን ወቅታዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በማደራጀት ጥልቅ (comprehensive)፣ አስተማማኝ እና ወቅታዊ የፋይናንስ መረጃዎችን ለዋና ኦዲተር፣ ለፓርላማ፣ ለምርመራና አቃቤ ህግ አካላት በማቅረብ የፋይናንስ ቁጥጥርን ውጤታማነት ለማጠናከር ካለው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው እንዳልሰሩ ያሳያል፡፡
- የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኂላ ግንባታ ሳይጀመር ለረጅም ጊዜ መቆየቱ በፕሮጀክት ውል እና ሂደት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ክፍተት እንዳለ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በቱሪዝም ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ለሙስና ስጋት የሆኑ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) ከነደረጃቸው እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

በጣም ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፦

- የፕሮጀክት አስተዳደር ላይ የሚሰጡ ድጋፎች፣ የስልጠናና የማማከር አገልግሎቶች እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎች የአሠራር ግልጽነት መጉደል/አለመኖር፣
- ከህገወጥ የእንስሳት ስምሪት (አደን) ጋር በተያያዘ ህግ ማስከበርና የጥበቃ ስራ (የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶች የተጠናከሩ ባለመሆኑ)፣

ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፦

- የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በበቂ መልኩ ያልተዘረጋ ከመሆኑ አንፃር የቅርስ ጥገና አሠራር ላይ ያሉ ክፍተቶች፣
- የፍቃድ አሰጣጥ ሂደት (ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ መመሪያ በወቅቱ ባለመዘጋጀቱ)፣
- የንብረት አስተዳደር አሰራር (ንብረቶችን በአግባቡ ካለመያዝና ካለመመዝገብ ጋር ተያይዞ የሚመጣ)፣
- የተለያዩ አገልግሎቶች ክፍያ አፈፃፀም (መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ከመፈጸም አንፃር የሚከሰት)፣
- የሰው ሃብት አስተዳደር ሥር ከሚገኙ የተለያዩ ሥራዎች መካከል ቅጥር፣ ዝዉዉርና ምደባ አሠራሮች ላይ ያሉ ክፍተቶች፣

ክፍል አምስት፦ ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፥-

- የፕሮጀክት አስተዳደር ላይ የሚሰጡ ድጋፎች፣ የስልጠናና የማማከር አገልግሎቶች እንዲሁም የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ ያለውን የአሠራር ግልፅነት መጉደል ተቋማቱ ውሎ ሳያድር ሊያርሙት ይገባል። በተመሳሳይም የቅርስ ጥገና አሠራር ሂደት ላይ ያሉ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት መፍትሔ ሊሰጡ ይገባል።
- ተቋማቱ የፍቃድ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ መመሪያ በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል በማፀደቅ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
- ከህገወጥ የእንስሳት ስምሪት (አደን) ጋር በተያያዘ፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በማጠናከር የህግ ማስከበርና የጥበቃ ስራ ውስጥ ያሉትን ብልሹ አሰራሮች ማምከን ይገባል።
- የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓቶች የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል፣ ምንጫቸው ያልታወቀ ንብረቶችን ለመለየት እና ሰፊ የህዝብ አገልግሎት ታማኝነትን ለመገንባት ሁለገብ መሳሪያ ናቸው። ስለዚህም የዘርፉ ተቋማት ይህን ስርአት በአፋጣኝ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
- የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በባለቤትነት የሚያስተባብሩ የሥራ ክፍሎች ሆነው እንደሚደራጁ ይገልፃል። ይህን ተልዕኮ በብቃት እንዲወጡ የሥነምግባር ክፍሎችን በተገቢው በጀትና የሰው ኃይል የተሟላ ማድረግ፣ ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር ያላቸውን ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር እንዲሁም የስራ ክንውናቸውን በበላይ ሃላፊዎች ማስገምገም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
- የፋይናንስ አሠራር ሂደትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ ፈጣንና ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር የዘርፉ ተቋማት ለተግባራዊነቱ አስፈላጊ ጥረቶችን ሊያደርጉ ይገባል።
- በሙስና ስጋት ጥናት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ አስፈላጊ ማሻሻያዎችን እና የእርምት እርምጃዎችን በወቅቱ የመውሰድ ባህል ማዳበር፣ እንዲሁም የተደረጉ ማሻሻዎችን ለማህበረሰቡና ግንኙነት ላላቸው ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ፣
- የተጠናከረ የፕሮጀክት/ኮንትራት አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከማድረግ አንፃር ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበትን አሰራር በመቀነስ፣ አስቀድሞ የፕሮጀክቶችን ዲዛይን በተገቢው በመገምገምና ከግንባታው ዓላማ አንፃር የሚሰሩ ስራዎች በአግባቡ የተካተቱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ ያለውድድር ተጨማሪ ስራዎች የሚሰጡበትን አሠራር በመቀነስ፣ እንዲሁም የኮንትራት አስተዳደር አቅምን በማሳደግ የግንባታ ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር እንዳይጋለጥ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።
- የፕሮጀክቶች በውሉ መሰረት በጊዜያቸው አለመጠናቀቅ እና የካሳ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ግንባታው ሳይጀመር ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ማድረግ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲሁም

የህዝብን ሃብት ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ በፕሮጀክት ውል፣ ሂደትና ርክክብ ላይ ጥብቅ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

- የዘርፉ ተቋማት አመራርና ሰራተኞች የታማኝነት፣ የተጠያቂነት፣ የፍትሃዊነት እና የመተማመን ጠንካራ የሞራል እሴቶችን እንዲያዳብሩ ባለመ መልኩ የሥነምግባር ስልጠናዎችን በመደበኛነት መስጠት ይጠብቅባቸዋል፡፡
- የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ በማከናወን ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ያለበቂ ዕውቀትና ችሎታ ተቋማቸውን በሚጎዳ ሁኔታ ተቀጥረው ከሚያገለግሉ ሰራተኞች የዘርፉን ተቋማት ማጥራት፣
- ከግዢ፣ ደንብና መመሪያ ጋር የተያያዙና ሌሎች መረጃዎችን በተቋማዊ ድረ-ገጽ ላይ የማኖር ባህልን ማጎልበትና ሰራተኞችና ሌሎች ተገልጋዮች እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣

ማጣቀሻ ፅሁፎች

1. Assaf, AG and Josiassen, A (2012), Identifying and ranking the determinants of tourism performance: a global investigation, J Travel Res, 51(4):388–399.
2. Das J, DiRienzo C (2010), Tourism competitiveness and corruption: a cross-country analysis. Tour Econ 16(3):477–492.
3. Ekine, Soala (2018), Corruption and Tourism: Evidence from democracies and non-democracies, Issues in Political Economy, 27(1):47-59.
4. Harris, LC (2012), Ripping off tourists: an empirical evaluation of tourists' perceptions and service worker (mis)behavior, Ann Tour Res 39(2):1070–1093.
5. Lv, Z and Xu, T (2017), A panel data quantile regression analysis of the impact of corruption on tourism, Curr Issue Tour, 20(6):603–616.
6. Maria, KK, Ioanna, S and Salomi, D (2022), Nonlinear nexus between corruption and tourism arrivals: a global analysis, Empir Econ, 63:1997–2024.
7. Méon, Pierre-Guillaume and Sekkat, Khalid (2005), Does corruption grease or sand the wheels of growth? Public Choice, 122(1):69-97.
8. Papathanassis, Alexis (2016), Combating Tourism-related Corruption: Effective Countermeasures Derived from Analysing Tourists' Perceptions and Experiences, https://stec.univ-ovidius.ro/html/anale/RO/2016/2016-II-full/s3/19.pdf
9. Poprawe, Marie (2015), "A Panel Data Analysis of the Effect of Corruption on Tourism", Applied Economics, 47(23): 2399-2412.
10. Tosun C and Timothy D (2001), Shortcomings in planning approaches to tourism development in developing countries: The case of Turkey, International Journal of Contemporary Hospitality Management, 13(7):352– 359.
11. UNWTO (2022), https://www.unwto.org
12. Yap, G and Saha, S (2013), Do political instability, terrorism and corruption have deterring effects on tourism development even in the presence of UNESCO heritage? A cross-country panel estimate, Tour Anal 18(5):587–599.